# ምረጥ/ቁረጥ!

ከዋኔና ከርግብ
ተንኰለኛው እባብ
ቢበልጥም በጥበብ
ተጠቅልሎ ከካብ
ኣፈር ይመገብ...




እንሽላሊት፣ እንሽላሊት!
ከልብ፣ ከኣንጀት ወተት
ከጉበት፣ ከኩላሊት
ነገ በእኩለ ሌሊት
ትቀምሻለሽ ብልት




ገበሎ! ገበሎ!
አትበላ በቆሎ
አትለብስ ደበሎ
አትሰግር በበቅሎ
ማን ሰጠህ ድንቡሎ?




ኻጉንቸር፣ ዕንቁራሪት
ከጉረሮ ከማንቁርት
በሌሊት፣ በውድቅት
በጆሮ-ደግፍ፣ ዕንቅርት
እንዳታልቁ በድርቀት!




ኣንበጣና ጊንጥ
ይብቃ ማላገጥ
ኑግና ሰሊጥ
እስክትላላጥ
አብረህ ተወቀጥ




ከአይጥ፣ ከድመት
ሕይወትና ሞት
ባጭር ብናትት
ዱለትና ሓሞት
ጾም መፍቻ ሙክት




አንተ ሸለምጥማጥ
አጣህ መላ-ቅጥ
ማ’ ብለህ ትመርጥ
ዓርፈህ ተቀመጥ
ሳትቀጠቀጥ!

ሸረሪት! ሸረሪት!
በኩራት፣ በዕብሪት
ገብተሽ ሽክርክሪት
እርር ብለሽ ቅርት
እንደ እሳት ክብሪት…

ገ.ኢ/ጎርፉ።






***Back to Meskot***

---

***The views reflected in the above poems are solely of the author and are not necessarily shared by Meskot. You may contact G.E. Gorfu for comments at gegorfu@yahoo.com.***